# ግልጽ ደብዳቤ

**መጋቢት 14፣ 2002 ዓ.ም**

**ለፕሬዚደንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት**
**አዲስ አበባ**

ክቡር ፕሬዚደንት

በመጀመሪያ መልካም ጤንነትን እየተመኘሁ የአክብሮት ሰላምታ አቀርባለሁ።

ይህንን ደብዳቤ የምጽፍልዎ ተራራ ላይ ወጥቼ እሪ! ኡ! ኡ! የሕግ ያለህ! እያልሁ እንድጮህ የሚገፋፋ ስሜት ሰንጎ ስለያዘኝና እግዚአብሔርና ኅሊናዬ ስላስገደዱኝ ነው እንጂ ላስቸግርዎ ብዬ አይደለም።

ወይዘሮ ብርቱካን ሚደቅሳ በመንገድ ላይ ተይዛ ከታሰረች አንድ ዓመት አለፋት፤ ጥፋተኛ ነች ወይስ አይደለችም የሚለው ክርክር ውስጥ አልገባም፤ የእኔ አትኩሮት መንፈሳዊ (ሞራል) ነው፤ የሕጉ መንፈስ ነው፤ ወይዘሮ ብርቱካን አንድ ሰው ነች፣ ማለትም ሰው በመሆንዋ መሠረታዊ መብቶች አሏት፤ ወጣት ነች፣ ማለትም ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው ከሚገኝበት ውስጥ ነችና የአብዛኛዎቹን ተስፋ አዝላለች፤ ሴት ነች፣ ማለትም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሃምሳ በመቶ ከሚያህለው ውስጥ ነችና የሴቶችንም ተስፋና የወደፊት ዕድል ታንፀባርቃለች፤ የሕግ ባለሙያ ነች፣ ማለትም በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት በሺህ ከሚቆጠሩት ውስጥ ነችና የሕጉን ሚዛናዊነትና አለኘታነት ታሳያለች፤ የአንድ አዲስ ፖለቲካ ፓርቲ መሪ ነች፣ ማለትም በጣት ከሚቆጠሩ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን ከመረጡት ሰዎች ውስጥ ነችና የሰላምን ቀንበር ተሸክማለች።

ይህች ሰው ለዚች ደሀ አገር የሰላምና የፍቅር መልእክተኛ፣ የልዩነታችንና የአንድነታችን መግለጫ፣ የጥንካሬና የሀብት ምንጭ ለመሆን የምትችል በአእምሮም በመንፈስም በጎውን መንገድ የመረጠች የሕግ ሰው ነች፤ ይህ ቢሆንም ከመንገድ ላይ ስትያዝ አብሬአት ስለነበርሁ የሆነውን ሁሉ አይቻለሁ፤ እኔም በሰደፍ ፊኛዬ ላይ ተመትቻለሁ፤ ከታሰረችም በኋላ ለአገርና ለወገን አደገኛ የምትሆን አስመስሉ ከሌሎች እስረኞች በከረረና በጠበቀ አኳኋን ከእናትዋና ከትንሽ ልጇ በቀር ሌላ ሰው እንዳያያትና እንዳይጠይቃት ተደርጋ፣ ራድዮ እንዳትሰማ ተከልክላ፣ መጻሕፍት እንዳይገባላት ሆኖ አስራ አራት ወራት ያህል አሳልፋለች፤ እንደማንኛውም እስረኛ ወዳጅና ዘመድ እንዲጠይቃት ፍርድ ቤት ቢወስንም እስከዛሬ ድረስ ይህ አልተቻለም፤ ወይዘሮ ብርቱካን በሕጉ ላይ ያላት እምነት በጣም ከፍተኛና

ጠንካራ ነው፣ ሕግ በሥራ ላይ የሚውለው ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ሲሆን በአገርና በወገን ላይ ያለውን እምነት ከማቀጨጩ በላይ መከራንና ስቃይን እጥፍ ድርብ ያደርገውና የመንፈስ ጭንቀትን ያስከትላል፤ ምን ዓይነት ወንጀል ፈጽማ ነው ወይዘሮ ብርቱካን ለዚህ ዓይነቱ ቅጣት የተዳረገችው? በማያጠራጥር መንገድ አገራቸውን የከዱ ሰዎች እንዲህ ያለው ቅጣት ያልደረሰባቸው እንደነበሩ እናውቃለን፤ ታዲያ የዛሬው ጭካኔ ከየት መጣ? አገርንስ እንዴት ይጠቅማል?

መጋቢት 12/2002 የወይዘሮ ብርቱካን እናት ወይዘሮ አልማዝ ገብረ እግዚአብሔር ልጃቸውን ለመጠየቅ ገብተው ወይዘሮ ብርቱካን እንደታመመች ስትነግራቸው የሰማችው የወህኒ ቤቱ ፖሊስ ተቆጥታ ብርቱካንን ወደክፍሏ እንድትገባ አስገድዳ እናቲቱንና ልጅቱንም አስወጣቻቸው፤ ይህ ድርጊት ለብዙ ጥርጣሬ በርን የሚከፍት ቢሆንም በበኩሌ ሕመምን ለእናት መንገር እንደክፉ ምሥጢር ማውጣት ተደርጎ የሚታይበትና የሚያስቆጣበት፣ የመጠየቂያውን ሰዓትም ለማቋረጥ የበቃበት አጥጋቢ ምክንያት የሚገኝለት አይመስለኝም፤ ብርቱካን ከታመመች ሕክምና የምታገኝበትን መንገድ ከመፈለግ የበለጠ ጥያቄን አያስነሣም፤ ይህም ሰብዓዊና ሕጋዊ ጥያቄ ይመስለኛል።

ወይዘሮ ብርቱካን ከእናትዋና ከልጅዋ ጋር ሁሉም እያለቀሱ ሲለያዩ እንባቸው መሬቱን አያደርቅም? ልጅ ለእናትዋ ሕመምዋን በመናገርዋ ብቻ የብርቱካን እናት፣ ብርቱካንና ልጅዋ፣ ሦስት ትውልድ ሲያለቅስ እግዚአብሔር አያይም? ዓለም አይታዘብም? ይህንን ሁነት በሰብዓዊነት ሚዛን፣ በመንፈሳዊና በጨዋነት ሚዛን፣ በሕጋዊነት ሚዛን፣ በታሪክ ሚዛን ሲመለከቱት የሦስት ትውልድ ለቅሶና ሐዘን የት ይደርሳል? የት ያደርሳል? የአገራችንን ስምና ታሪክ ከእያንዳንዳችን ስምና ታሪክ ለይተንም አገናኝተንም በማየት ወደትክክለኛና ሚዛናዊ ውሳኔ ልንደርስ እንችላለን፤ ይህንን መንገድ እንዲያመለክቱንና ለወይዘሮ ብርቱካን ሕክምና መንገድ እንዲከፍቱ በኢትዮጵያ አምላክ እማጸንዎታለሁ።

ትሑት ታዛዥዎ

መስፍን ወልደ ማርያም